# ታዛ

ስምንት
ጥያቄዎች
ለተሸላሚው
ባለብሩሽ





በቼክ የካርል
ሮቦት 100ኛ
ዓመት ተከበረ

ቅፅ 04 ቁጥር 39 ህዳር 2013 ዓ.ም.
ወርሃዊ የባህል እና የጥበብ መጽሔት
ዋጋ 20 ብር

# በሽምግልና

## ባህላችን ላይ የተጋረጡ ተግዳሮቶች





# ሮቦት – ዝነኛው ቼካዊ 100ኛ ዓመቱን ያከብራል

በያሮስላቭ ቫይስ

ከመቶ ዓመታት በፊት በራሺያና ቤላሩስ ድንበር አቅራቢያ ፔትሮቪች በመባል ከምትታወቀው መንደር፣ የአይሁድ ዝርያ ካለው አዚሞቭ ቤተሰብ ተወለደ። ትክክለኛ የልደት ቀኑ አይታወቅም። እ.አ.አ. ከ1919 ጥቅምት እስከ 1920 መጀመሪያ አካባቢ ነው ተብሎ ይታሰባል። ይሁንና RMS Baltic ተብላ በምትታወቀው መርከብ እ.አ.አ. በ1923 ከአዲሲቷ ሶቪየት ሕብረት ወደ ኒውዮርክ የመጡት የልጁ ቤተሰቦች፤ የሦስቱ ልጆቻቸው አንጋፋ የሆነውን ልጃቸውን እ.አ.አ. ጥር 2 ቀን 1920 ተወለደ በሚል የልደት ምስክር ወረቀት አሰጠው። ስሙንም ‹‹ዜድ››ን ወደ ‹‹ኤስ›› በመቀየር፤ አዚሞቭን ወደ አሲሞቭ አዛወረው። ኢሳቅ አሲሞቭ በኋላ ላይ ዝነኛና በዓለም እጅግ ታዋቂ ለመሆን በቃ።

ልጁ በተወለደበት ተመሳሳይ ጊዜ የሠላሳ ዓመቱ የአዲሲቷ ቼኮዝሎቫኪያ የጥበብ ኮከብ የነበረው ካሬል ቻፐክ ፕራግ ብሔራዊ ቲያትር ስለሚቀርብ አዲስ ድራማ እያሰበ ነበር። ጀግኖቹንም ገጸ-ባሕሪያት ‹‹ሰው ሠራሽ ሠራተኞች›› ወይም ‹‹ሕይወት ያላቸውና የማሰብ ችሎታ ያላቸው የሚሠሩ ማሽኖች›› እንዲሆኑ አቀደ። ማሽኖቹን ስም ለመስጠት አእምሮውን አስጨነቀ። ሌበር (Labor) የሚል የእንግሊዝኛ ቃል መጣለት፣ (የእንግሊዘኛው ሌበር የሚለው ቃል ሥረ-መሠረቱ ላቲን ሲሆን፤ ሥራን ከመግለጹም ባሻገር፤ ከባድ ሥራን፣ ጥንካሬን፣ ድካምና ሕመምን ይገልጣል) ቢሆንም ፈጽሞ አልረካበትም። ጥርጣሬውን ለታላቅ ወንድሙ አወያየው ። ዮሴፍ ቻፐክ የተከበረ ሠዓሊ ነበር። አብረው ጥቂት ነገሮችን ጽፈው ስለነበር፣ ካሬልም ብዙ ሐሳብ አካፍሎት ነበር። "ሮቦት በላቸው" ብሎ ብሩሽ ነክሶ በያዘው አፉ እያንሾካሾከ መሣሉን ቀጠለ። "ይኸው ነው" ሲል ካሬል ቻፐክ እራሱ በኋላ ላይ ሁኔታውን ገልጾታል። ቃሉ ስላቪክ መሠረት ሲኖረው ሠራተኛ የሚል ተመሳሳይ ትርጓሜ አለው። በእርግጥ ሠራተኛ ከሚለው ትርጓሜ በላይ ኃይለ-ቃልነት አለው።

ካሬል ቻፐክ እ.አ.አ. በ1920 በመጀመሪያ አር.ዩ.አር.ን (R.U.R.) መጻፍ ጀመረ። (የቲያትሩን ስም የሠየመው ድርጅት ሙሉ ስም ‹‹የሮሱም ዓለም አቀፍ ሮቦት›› (Rossum's Universal Robots) ይባል ነበር) ይህም አሳቤው በዓመቱ መጨረሻ በፕራግ ብሔራዊ ቲያትር በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታይ ነበር። ስለዚህም እ.አ.አ. በ1920 ሕዳር ላይ አቨንቲነም በሚባል አሳታሚ



ድርጅት አማካኝነት በዮሴፍ ቻፐክ የሽፋን ገጽ ሥራ ታተመ። ያም ሆኖ ዋናው የታቀደው እቅድና ሐሳብ ቀርቶ፣ ጀማሪ የቲያትር ቡድን አባላት የሆኑ ህራደትስ ክራሎቬ አውራጃ ከተማ የሚኖሩ ተዋንያን የራሳቸውን ቲያትር ሠርተው አቀረቡ። ጀማሪዎቹ ተዋንያን ቲያትሩ በብሔራዊ ቲያትር የሚታይበትን የመጀመሪያ

ምሽት መጠበቅ ተሳናቸው። እናም እ.አ.አ. ጥር 2 ቀን 1921 የሮሱም ዓለም አቀፍ ሮቦትን በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ በጀማሪ ተዋንያን፣ በብሔራዊ የባቡር ድርጅት ተቆጣጣሪ አዘጋጅነት በክልሉ መድረክ ላይ ተሠርቶ ቀርቧል። ቼክ ብሔራዊ ቲያትር መድረክ ላይ የቀረበው ከሦስት ሳምንታት በኋላ እ.አ.አ. ጥር 25፣ 1921 ነበር። ነገር ግን ለሚቀጥሉት ስድስት ተከታታይ ዓመታት ዝግጅቱ ሲቀርብ ትኬቶች በጥቁር ገበያ ጭምር ይሸጡ ነበር።

እንደ ኢሳቅ አሲሞቭ ሁሉ የቻፐክም ሮቦት ወደ ኒውዮርክ የተወሰደው ቀደም ሲል ነበር። እንዲያውም ከትንሹ ኢሳቅ አራት ወራት ቀድሞ ነበር አሜሪካ የደረሰው። የመጀመሪያው የሮሱም ዓለም አቀፍ ሮቦት ለመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካ ውስጥ የታየው እ.አ.አ. ጥቅምት 9 ቀን 1922 በብሮድዌይ ጋሪክ ቲያትር፣ በትያትር ጊልድ ነበር።

የቻፐክ "ስብስብ ድራማ በመተዋወቂያ ኮሜዲና በሦስት ገቢሮች ውስጥ" የሚለው የአር.ዩ.አር. (R.U.R.) ንኡስ ርእስ ሲነበብ ወዲያው መነጋገሪያ ሆነ። ስሜት ሰጪ ሆነ። ቻፐክ ዘመኑን የሚዋጅ ርእስ አግኝቷል። የቴክኖሎጂን ማኅበረሰብ አፍራሽ ሚና የሚዳስስ (በሌሎች ሥራዎቹ ላይ እየተደጋገመ የሚነሣ ጭብጥ የሆነ) እና በተመሳሳይም በራስ ለሚተማመኑ፣ በጨካኝ ተግባራቸው ለሚታወቁ ምሁራንና ከስግብግብ ቱጃሮች፣ ለሐሳብና ዕሴት ቦታ ስለማይሰጠው ዘመናዊነት አድናቆት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

ተለዋጭ ዘይቤው የተለያዩ ትርጉሞች ነበሩት። ከራስ-ወዳድ ካፒታሊዝም ከባድ ትችት አንሥቶ፣ እስከ ተቃራኒው የአመፅና የአብዮት ስጋቶች ጉዳይ ድረስ ደራሲው ሊያስጠነቅቅ የፈለገው ነው። ለአንዳንዶቹ የተውኔቱ ዋና ገጸ-ባሕርይ ሰዎች ሲሆኑ፣ ለሌሎቹ ደግሞ ሮቦቶች ነበሩ።

100 ዓመት ወደ ኋላ ዞር ብለን ስናይ በቻፐክ ዘይቤዎች ዙሪያ፣ አዳዲስ ትርጓሜና እውነታዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። የሮሱም ዓለም አቀፍ ሮቦት ድርጅት በዛሬ ዓይን መታየት ያለበት እንደ ዓለም አቀፍ ባዮቴክኖሎጂ ድርጅት ነው። ዓለም አቀፍ ልኬቱም ከንብረት፣ ከፈጠራ ሥሪትና ተጽዕኖ አንጻር ሲታይ፣ ለዛሬዎቹ ለጉግል፣ አፕልና ቴስላ ባንድነት መፈጠር መሠረቱ ይሆናል። ድራማው ላይ ዋነኛዋ ጀግና ሴት ገጸባሕሪ ሆና የምትተውነው ሄለን ግሎሪ፣ እንደዛሬ ዘመኑ ዓለም አቀፍ የሰው መብት ተቆርቋሪ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ተምሳሌት ናት። ሮቦቶች በሰው የተፈጠሩ ሲሆኑ፣ እነሱን የፈጠሩትን ፍጡር ሰውን ከማጥፋታቸውም በላይ፣ ዛሬ በሰው የተፈጠሩ የፈጠራ ውጤቶችና ምርቶች አልፈውም ዓለምን እራስዋን ለማጥፋት ከሚያስችላቸው ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

ምንም እንኳን በቲያትሩ ዙሪያ ሲቀርቡ የነበሩ ሂሶች ውዳሴ ያበዙ የነበረ ቢሆንም፣ ሁልጊዜም እንዲያ አልነበሩም። በቼኮዝሎቫኪያ በተለይ ደግሞ የግራ ባህላዊ አቫንት-ጋርድ (የምሁራን ስብስብ) "አዲስ ነገር ማምጣት ያቃተዉ፣ አማላይ ርእስ ተጠቃሚ፣ ውስብስብ ግን የወረደ ሥራ፣ የውጭ አገር ተደራስያንን ለማስደሰት የተፈጠረ ሥራ..." ብለው ቻፐክን ተችተውታል።

ምንም እንኳን የደራሲው የመጀመሪያ እቅድ ያ ባይሆንም፣ የሆነው ግን እንዲያ ነበር። አር.ዩ.አር. (R.U.R.) ቲያትር በሄደበት ሁሉ ተወደደ። ድራማው አሽን (ጀርመን) በ1921 መጀመሪያ ከታየ በኋላ በዓመቱ ዋርሶው፣ ቤልግሬድና አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ኒውዮርክ ላይ ታይቷል። እ.አ.አ. በ1923 በለንደን፣ በቪየና፣ በበርሊን፣ በዙሪክና በቀጣዩ ዓመት በፓሪስ፣ በቶኪዮ፣ በቡዳፔስትና በክራኮው ታይቷል። በተመሳሳይ ዓመታት ዉስጥ ወደ ብዙ አውሮፓውያን ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን፣ በቅርቡ ደግሞ እንደ ፊሊፒንስና ታይላንድ በመሳሰሉት አገሮች ተውኔቱ ታይቷል።


ድራማው በታዋቂው የዓለሞች ጦርነት (War of the Worlds) መጽሐፍ ደራሲና በጊዜው በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም ተጽዕኖ ፈጣሪ በነበረዉ ምሁር በኤች ጂ ዌልስ (H G Wells) የተንቆለጳጰሰ ሲሆን፣ ምሁሩ ኋላ ላይ ድራማው ለኖብል ሽልማት እንዲታጭም ቅስቀሳ አድርጓል። እ.አ.አ. በ1938 አር.ዩ. አር. (R.U.R.) የመጀመሪያው የቢቢሲ ተከታታይ ሳይንሳዊ ልቦለድን መሠረት ያደረገ የቴሌቪዥን ድራማ ፕሮግራም ለመሆን በቅቷል።

ድራማው የዓለምን መድረክ በግምባር ቀደምነት ሲቆጣጠር፣ ቼክ የተወለደው «ሮቦት» የሚለው ቃል ደግሞ፣ የዓለምን ባህላዊ አውድ ብቻ ሳይሆን፣ ሳይንሳዊና ሕዝባዊ አውታሮችንም ጭምር ሊቆጣጠረው ችሏል።

ከሰው ሌላ ዓለም አቀፍ ዝነኛ መሆን አይቻልም የሚለው ተቀይሮ፣ ሮቦት ዓለም አቀፍ ክሥተትና እየጨመረ ለመጣው ኃያል የቴክኖሎጂ ሥልጣኔ ምልክት ሊሆን ችሏል።

ይሁንና ለሮቦት ፕላኔታችን ላይ መብዛት አስተዋጽዖ ያደረገው የሮቦት አባት የሚባለው ካሬል ቻፐክ ብቻ አይደለም። በ30 ዓመት ዕድሜ የሚያንሰው ኢሳቅ አሲሞቭ እንደ አሳዳጊ አባትነቱ ትልቅ ዋጋ ሊኖረው ባይችልም አስተዋጽዖ ግን ነበረው።


የብሩክሊን ከረሜላ መደብር ባለቤት ልጅ የሆነው ኢሳቅ አሲሞቭ፣ ሥነ እንስሳ (Zoology) በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ማጥናት ቢጀምርም፣ በቦስተን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ት/ቤት ለብዙ ዓመታት ሲያስተምር በነበረው ባዮ-ቴክኖሎጂ ዲግሪ ተመረቀ። ሳይንስ ፊክሽንን በጥራት መጻፍ ከመጀመሩ በፊት በልጅነቱ ዘመንም ይሞነጫጭር ነበር። የመጀመሪያው አጭር ልቦለዱ "ሩቅ የተተወቸው የሮማ ሴት አማልክት" የሚለው እ.አ.አ. በመጋቢት 1939 "አስገራሚ ታሪኮች" ላይ ታትሞለታል። በዛው ዓመት ሰኔ ላይ «ሮቢ» የተሰኘ ስለ ሮቦት የመጀመሪያ የሆነውን አጭር ልቦለድ




ጽፎ፣ እ.አ.አ. መስከረም 1940 ሱፐር ሳይንስ ላይ ታትሞለታል። የመጽሔቷ ዋና አዘጋጅ ፍሬድሪክ ፖል የድርሰቱን ርእስ ቀይሮ "ፕሌይ ፌሎው" ሲለው አሲሞቭ በጭራሽ ይሄን ስያሜ አልወደደውም ነበር።

የድርሰቱ ዘውግ ማጠንጠኛ ማእከል፣ እ.አ.አ. በ1940ና በ1950ዎቹ ዓመታት አሜሪካ ውስጥ በጭርንቁሱ መንደር ነዋሪ የሆኑ፣ ፊታቸውን ብጉር የሞላውና ሐሳባቸውን ለልጃገረዶች መግለጽ የተሳናቸው ወጣቶች የሚገለጹበት ክፍለ ዘመን ነበር። ይህም ጭብጥ በሁለቱ አሜሪካዊያን ደራስያን በሮበርት ኤ ሃይንላይንና በኢሳቅ አሲሞቭ የተጻፈበት ዘመን ነበር። የቅድስት ሥላሴ ሳይንሳዊ ልቦለድ ወርቃማ ዘመናት (እ.አ.አ. 1938-1946) በብሪታኒያው ጸሐፊ በአርተር ሲ ክላርክ በወቅቱ ተወድሷል።

አሲሞቭ ወደ ታሪክ ዘውግ ሲያመራ፣ ከሁለት ጭብጦች አንጻር ነበር። በተከታታይ ይወጡ ከነበሩ መጽሐፍት ከረዥምና ውስብስብ መሠረት ያላቸው መጻሕፍት ጭብጥ ይልቅ፣ ተከታታይ የሮቦቶች ታሪኮች መጻፍ ላይ ያተኩር ነበር። ደርዘን የሚሞሉ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስቦች እንደ Collection I፣ Robot from 1950፣ The Steel Cave ረዥም ልቦለድ (1954 )፣ The Naked Sun (1957)፣




**ቻፔክ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚያስብ ፈጣሪ ያውቃል። ምናልባትም ግድ ላይሰጠውም ይችላል። ሁለቱ ሰዎች የሚለያዩት በአጠቃላይ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፣ በባህል ልምዳቸውና እይታቸውም ጭምር ነው።**

Robots from Dawn (1983) እና Robots and Empire (1985) የታተሙለት ሥራዎቹ ናቸው።

ለማንኛውም ዓይነት ዘርፍ ወሳኞቹ የዘርፉ ፈጣሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ዘርፉን የሚያዳብሩትና የጐደለውን የሚሞሉና ለማሻሻል የሚጥሩ ሰዎችም ጭምር ናቸው። አሲሞቭ ያደረገውም ይህንኑ ነው። እርግጥ የድሮውን ሰው ሠራሽ ማንነቶች ጭብጥ ወይም ተንቀሳቃሽ ማሽኖችን (እንደ ሆምንኩሲ፣ አንድሮይድ፣ አውቶማተን) ከቻፔክ ሮቦት ጋር በመቀላቀል ከራሱ የመነጨውን ሳይንሳዊ ሮቦት አበልጽጓል። ከሕግ ይልቅ ተፈጥሮን መመርመር በሚችለው አእምሮው ሦስት ሕጎችን ማለትም ሰዎችና ሮቦቶች በሰላም አብረው ሳይጣሉ የሚኖሩባት ዓለምን ያለ ቅድመ-ሁኔታ አስቀምጧል።

1ኛ ሕግ፡- ሮቦቶች የሰው ልጅ ላይ ጉዳት ማድረስ የለባቸውም። የሰው ልጅ እንዲጎዳ መፍቀድና ሲጐዳም እያዩ በዝምታ ማለፍ የለባቸውም።

2ኛ ሕግ፡- ሮቦቶች የመጀመሪያውን ሕግ ካልተቃረኑ በስተቀር የሰውን ልጅ ትእዛዝ ማክበር አለባቸው።

3ኛ ሕግ፡- ሮቦት 1ኛና 2ኛውን ሕግ ሳይፃረር የራሱን ህልውና መጠበቅ አለበት።

አሲሞቭ እነዚህን ሕጎች ሲያወጣ አንድ መሠረታዊ እርምጃ ወስዷል። ሮቦት እንደ አርቲፊሻል አካል ለሰው ልጅ ከስጋትነት ይልቅ ወዳጅ፣ ጠባቂና አገልጋይነትን ማላበስ ነው። በፖለቲካ አውዳዊ ፍቺ የሰው ልጅ ፊት ያለው ሮቦትና በተመሳሳይ ጊዜ ከሶሻሊዝም ጋር ባለን የፖለቲካ ልምድ አኳያ፤ ሙከራው ጥሩ ቢሆንም ግን ጊዜያዊና ያልተሳካ ነው። ያ ደግሞ ከአንድ እስከ ሦስት ብቻ ማሳያዎችና መቋጫዎች አልነበሩም።

ለዚህ ነው የአሲሞቭ ሕጎች እስካሁን የሚጠቀሱና እንደገና ተሻሽለው፣ ተጨምሮባቸው አሁን ካለው የዓለም ሁኔታ ጋር በልቦለድ ብቻ ሳይሆን፣ ከእውኑ ዓለም ተጨባጭ እውነታ ጋር ተሰናስሎ ሮቦቶቹ ቀስ በቀስ እየተቀየሩ የመጡት። ሮቦቶች በአሁኑ ጊዜ የምርት መጋዘን፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የቲያትሮችና የማእድ ቤት ክፍል አካላት ናቸው። ሮቦቶች እንደ ጓደኞቻችን ናቸው። ልክ እንደ የቻፔኮቹ ፕሪመስና ሄሌና ወይም እንደ አሲምቮቹ ሮቢና ዳንኤል ኦሊቫው አሁንም ልቦለዶች ናቸው።

ኢሳቅ አሲሞቭ ሁልጊዜ የሮቦቶችን ከቼክ መምጣትና የቻፔክን ድርሰት ምንነት ይጠቅሳል። በሮቦት ታሪኮቹ ላይ ሳይሆን በታወቁት የሳይንስ መጽሐፍቶቹ ላይ ጠቅሷቸዋል።

ያም ሆኖ ቃለ-ተውኔቱ ተጽዕኖ አላሳደረበትም ወይም ፈጽሞ አልወደደውም ማለት እንችላለን። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ይህን መረጃ ቀጥታ ያገኘው ከራሱ ከአሲሞቭ ነው። እ.አ.አ. በ1988 መጨረሻ ከማንሀተን ሴንትራል ፓርክ በላይ የሚገኘው የሕንጻው ጫፍ ላይ ካለው ቤቱ ተገኝቶ ጐብኝቶታል። የቻፔክን ቃለ-ተውኔት ወዶት ይሆን እንደሁ ጠየቀው። በመልሱም ድርሰቱ ይሄ ነው የሚባል ተጽዕኖ እንዳላሳደረበት ገልጾለታል። እንደ እርሱ አመላለስና አባባል፤ ሐሳቡ ጥሩ ቢሆንም፣ የድርሰቱ ዋናው ጭብጥ ሮቦቶቹ አልነበሩም ባይ ነው። ቢያንስ ርእሱ ውስጥ ተወዳጅና አስፈላጊ የሚያደርገው ነገር አልነበረበትም ባይ ነው።

ቻፔክ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚያስብ ፈጣሪ ያውቃል። ምናልባትም ግድ ላይሰጠውም ይችላል። ሁለቱ ሰዎች የሚለያዩት በአጠቃላይ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፣ በባህል ልምዳቸውና እይታቸውም ጭምር ነው።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን እንደ ኮሎምቢያው የስላቪክ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ መምህር ዊልያም ኢ.ሀርኪንስ አባባል፤ ቻፔክ ከተውኔት ሥራዎቹ ሁሉ ዝቅተኛ ዋጋ የሚሰጠው ለዚህ ሥራው እንደሆነ አስምሮበታል። እንደ ፕሮፌሰሩ አባባል ከሆነ ቻፔክ ከRUR ጋር ያለውን ግንኙነት ማቋረጡን ጠቅሶ፤ እንደ ማስረጃም ለጋዜጣ በሰጠው ቃለ-ምልልስ ላይ፤ ቃለ-ተውኔቱን ማንም ሊጽፈው ይችል ነበር ያለውን ይጠቅሳል። ይህም ለተውኔቱ ዝቅ ያለ ግምት መስጠቱን ያሳያል ማለቱ ይጠቀስለታል።

ምናልባት ማንም ሊጽፈው ይችላል፣ ግን እሱ ጻፈው። ምስጋና ለእርሱ ይድረሰውና ከ100 ዓመታት በፊት ፕራግ ውስጥ የተፈጠረው «ሮቦት» የሚል ቃል፣ የሁልጊዜም የቼክ ታዋቂ ፍጡር ሆኗል። በኒውዮርክ ኢሳቅ አሲሞቭ ድጋሚ ትርጉምና እገዛ፣ ሮቦት፣ በዓለም ላይ እጅግ ጠቃሚ፣ ዘመናዊና ትውፊታዊ እሳቤ (ሚት) ያለው ቃል ለመሆን በቅቷል። በቴክኖሎጂ እድገትም ምክንያት ሮቦት ከምናብነት ወደ እውናዊነት ሊቀየር ችሏል።

## ማስታወሻ

ያሮስላቭ ቬይስ ቼካዊ ጸሐፊ፣ ተርጓሚ፣ አምደኛ፣ የፖለቲካና የሚድያ አማካሪ ነው። አያሌ ሳይንሳዊ ልቦለዶችን፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ ጸሐፍት ሥራዎችን ተርጉሞ አሳትሟል። እ.አ.አ. በ1994 ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በሚያመቻቸው ለተከበሩና የላቀ የሥራ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ጋዜጠኞች በሚሰጠው የትምህርት ዕድል ተሳታፊ የነበረ ነው። የቼክ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የፕሬዝደንቱ ዋና አማካሪ ሆኖ ከአሥር ዓመታት በላይ አገልግሏል። በአሁኑ ጊዜ በፕራግ ከተማ በመኖር ላይ ይገኛል።

ትርጉም- በናትናዔል ክበደና አበሩ ሰማ